# የጥላሁን ሕይወቱ ብቻ ሳይሆን ሞቱም አንድነትን እያስተማረን ነው።

ንጋቱ ያየህ ይራድ
ዳላስ ቴክሳስ

ስለ ጥላሁን ብዙ ተነግሯል ብዙ ተወስቷል። ልባቸው በሃዘኑ የተነካ ወጣትና ሽማግሌዎች ሳይቀሩ ባገኙት መንገድ ሁሉ ስሜታቸውን ሲገልጹም አስተውለናል። ገጣሚዎች እንደ አሸን የፈሉበት ተራኪዎች፣ ኪነተኞች በሙያቸው ያወደሱት ተባብረው ያዘኑበት በሥራው መኩራታቸውን ያረጋገጡበት ወቅት ቢኖር የዚህ ታላቅ የኪነት ሰው ሞት ነበር ተብሎ ቢነገር ስህተት አይመስለኝም። መታመሙን እያወቅን ይሞታል የሚለውን ለመቀበል አለመቻላችን የፍቅራችንን የመውደዳችንን ሃያልነት የሚያሳይ እንጂ እውነታን መካድም አልነበረም። ጥላሁን የሁላችንን ልብ የነካ በትዝታ ማእበል ያስዋዠቀን በደስታ ያስፈነጠዘን በሃዘን ያፈቃቀረን የኪነት አባት ነበር።

የጥላሁን የሕይወት ዘመን ችግር ያልነበረበት ነበር ብሎ መናገር ባይቻልም የሞተን መንቀፍ ደግሞ ባህላችን ባለመሆኑ ብሎም የዘመናት አገልግሎቱ ሁሉንም ስህተት ይደመስሰዋል በማለት በጥንካሬው እየኮራን እንድናስታውሰው ሆነናል።

ልብ ላይ ነው ወይንስ ሳንባ?
ወዴት ይሆን የፍቅር አንባ?

ብሎ የዘፈነውን የሚያስብ ወጣት የእውነትነቱ ነገር ብቻ ሳይሆን መልስ አለመስጠቱ ቢያሳስበው አይገርምም።

አትመልከች ሱፍ አትይ መኪና፣
እኔም እገዛለሁ እድሌ ሲቃና።

የሚለውን ያዳመጠ ወጣት ደግሞ የደረሰበት ትዝ እያለው አይኑ እንባው ቢያቀር ሁላችንም የምንጋራው ነውና የምንገረም አይመስለኝም ። ይህ ትውልድ እኮ በcow boy በምእራባዊ የረኛ ፊልም ያደገ የሕንድ ፊልም ከራሱ ኑሮ እያዛመደ mother Indianን እስካሁን እንደ ፍቅር እስከ መቃብር ቃል በቃል የሚያስታውስ እንደ ሆነ መዘንጋት የለብንም። በጥላሁን ሞት የተጎዳነው ሁላችንም ነንና ሁላችንም እግዜር ያጥናችሁ መባል ያለብን ይመስለኛል። ይህንን ስል የባለቤቱን የልጆቹን ብሎም የመላ ቤተዘመዶቹን ጉዳት ለማቃለል አለመሆኑን ልግለጽና ጥላሁን የሁላችን ስጦታ ጥላሁን የሁላችን ሃዘን መሆኑን ለማጠናከር እወዳለሁ።

ዛሬ የዚህ ጽሑፍ መነሻ ግን የተባለውን ለመድገም ስለ ጥላሁን የቀብር ስነስርአት ለማውሳት ብሎም ስለመስቀል አደባባይ የሐዘንተኛ ብዛት ለመናገር ሳይሆን ሐዘኑን አስመልክቶ ስለተደረገ የውጭ ሃገር ዘገባ ለመተረክ ነው። ጉዳዩ እነሆ የጥላሁንን ሞት በተመለከተ የኤርትራ ቴሌቪዥን በአማርኛ ፕሮግራም ያስተላለፈውን ልዩ ፕሮግራም አንድ በምእራብ አሜሪካ የሚኖር ጓደኛዬ በድሕረ ገጽ ላይ ተመልክቶ እኔም እንዳየው ላከልኝና ስመለከተው በጣም ስለተገረምኩ ሁኔታውን ለናንተ ለማካፈል ነው። ፕሮግራሙ በኤርትራውያን መዘጋጀቱን ማወቅ የሚቻለው ከቪዲዮው ላይ ያለውን ERI TV በማየት ብቻ ይሆናል። የፕርግራሙ አቅራቢ አማርኛን በጥናት ሳይሆን አፍ የፈታበት ቋንቋው ለመሆኑ ከማዳመጥ በስተቀር ምስክር አያስፈልግም። የቃላት አቀነባበሩንና አሰካኩን ያዳመጠ ደግሞ ጎበዝ ከማለት በስተቀር ምንም ማለት የሚችል አይመስለኝም። ግን አማርኛ ዘፈን ከተከለከለበት ሀገር ስለ አማርኛ ዘፋኝ መተረክ ብቻ አይደለም ታሪኩን ከቪዲዮ ጋር አቀነባብሮ ማቅረቡ ግን ከልብ ገረመኝ።

ፕሮግራሙ የሚጀምረው

ያሳለፍነው ጊዜ ደስታን ያየንበት፣
ተመልሶ ቢገኝ አሁን ምን አለበት።

በሚለው ዘፈን መሆኑ ያጋጣሚ ይሆን? ወይስ የሃገራችን መለያየት ያመጣውን ችግር ለማንሳት የታሰበ ይሆን አልኩና እራሴን ጠየቅሁ? መልስ ማግኘት እንደማልችል ደግሞ ልቤ ያውቀዋል። ስለ ጥላሁን ሞት የተሰማቸውን ሐዘን እነዲገልጹ እነ በረከት መንግስተ አብ ሳይቀር ቀርበው ተጠይቀው ነበር። ሁሉም ስለ ጥላሁን ትልቅ የኪነት ሰው መሆን መስክረዋል የተሰማቸውን ሐዘንም ገልጸዋል። የድሮ ትዝታቸውን አውግተዋል። ለኢተዮጵያ ሕዝብና ለቤተሰቡ የሐዘን ማጽናኛ አስተላልፈዋል። በመጨረሻ የገረመኝ ግን ይህ “ለኢትዮጵያና ለምስራቅ አፍሪካ ሕዝብ ጉዳት ነው” ሲሉ ማዳመጤን አልወደድኩትም። ምስራቅ አፍሪካን በኤርትራ ምትክ ያስገቡት ያለ ምክንያት እንዳልሆነ ግን ለመገመት ጊዜ አልፈጀብኝም። በሁኔታው አዘንኩ። ለመናገርም ለሃዘንም ፖለቲካዊ ትክክል ለመሆን የሚደረግ ጥንቃቄ እንደሆነ ተሰማኝ። ያም ሆኖ ግን የኤርትራ ሕዝብ እንዳዘነ ከካሜራው ጀርባ ከመጋራጃው ባሻገር ማየት ይቻል ነበር። “የኢትዮጵያ መንገስት የጥላሁንን ቀብር ያሳመረው ለፖለቲካ ብሎ ነው” ያሉኝን ግለሰቦች ያልኳቸው ትዝ አለኝ። በስልጣን ላይ ያሉት ባለስልጣናት እንደናንተው እንደኔም ጥላሁንን እየሰሙ ማደጋቸውን አትዘንጉ የሚል ነበር። አሁንም ፕሬዚዳንት ኢሳያስም እንዲሁ መሃመድ ወርዲን ጥላሁን ገሰሰን እየሰሙ ያደጉ ናቸው ብለን ለሰኮንድ እንኳን እናስብ። ትዝታ እኮ መጥፎ ነገር ነው። በመጨረሻ ፕሮግራሙን ያዘጋጀው ጋዜጠኛ ፕሮግራሙን ሲደመድም ያሰማው የጥላሁን ዘፈን እንዲሁ ያጀማመሩ ተቀጥላ ነበር።

መለያየት ሞት ነው ለተዋደደ ሰው፡
ስቃዬን አሳየኝ ደርሶብኝ ብቀምሰው።

እውነትም ኪነትና ስፖርት ድንበር አያግደውም። ጥላሁን ከሞተም በኋላ ድንበር ጥሶ አገር አቋርጦ ህብረትን ፍቅርን ሰላምን ለማምጣት ይጥር ጀመር። አንድ የማከብረው ዛሬ በሕይወት የሌለ ጔደኛዬ ያጫወተኝ ትዝ አለኝ። የመቃብር ቦታ ሲጎበኙ በሃውልቱ ላይ የተጻፈውን ጥቅስ አስታውሶ ከሁሉም ትዝ የሚለው “እንደናንተው ነበርን እንደኛ ትሆናላችሁ” የሚለው እንደነበረ መናገሩ ትዝ ይለኛል። እኔም እሱ ካለው ልነሳና ስንሞት ብቻ ሳይሆን በሕይወትም እያለን ለመከባበር ለመፈቃቀር እንሞክር።

ሙዚቃና ስፖርት ድንበር የለውም ማለትን ከተቀበልን የሕዝብን እንቅስቃሴ ለመግታት የሚፈልግ መተማመን የጎደለው ብቻ ነው ለሚለው ድምዳሜ የምንስማማ ይመስለኛል።

የሚቀጥለው የምንሰማው የጥላሁን ዘፈን እሩቅ ምስራቅን በአስመራ ተከተን፡

አስመራ ላይ ሳለሁ ወጣቷን ወድጄ
ትዝ ትለኛለች በፍቅሯ ነድጄ።

ይሆን ይሆናል ማን ያውቃል። ብቻ መሰንበት ደግ ነው፣እድሜ ይስጠን።